# ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ መርቆሬዎስ ተገድለው መናፍቁ መልከጸዴቅ ሊሾሙ ነው!

ከሦስት ቀን በፊት "በሲኖዶስ የጳጳሳት ሹመት ላይ የተነሡ ተቃውሞዎች ሲፈተሹ!" በሚል ርእስ አንድ ጽሑፍ ማስነበቤ ይታወሳል፡፡ በዚህ ጽሑፌ ላይ አባ ወልደትንሣኤ ስለተባሉት መናፍቅ ኑፋቄዎቻቸውን ምንም እንደማላውቅና ሰውም ሲያነሣ ሰምቸ እንደማላውቅ በመግለጽ ጵጵስናው እንደሚገባቸው ገልጨ ነበር፡፡ ይሄንን ያደረኩበት አራት ምክንያቶች ነበሩ፡፡ሁለቱን እነግራቹሀለሁ ሁለቱን ግን አሁን አልነግራቹህም፡፡ ጊዜያቸው ሲደርስ እኔ ሳልነግራቹህ እራሳቹህ የምትረዱት ይሆናል፡፡

አንደኛው ምክንያቴ የነበረው ከዚህ ቀደም በስደት ላይ ስላለው የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ስላንዣበበበት አደጋ ጉዳይ ሁለት ጽሑፎችን ጽፌ ነበር፡፡ መናፍቃኑ ግባቸው እንዳይሰናከል ጉዳቸው እንዳይታወቅ ሁለቱንም ጽሑፎች በየድረገጾች ከመለጠፋቸው ከየ ድረገጹ ለቅመው እንዲነሡ እንዲወገዱ ሲያደርጉ አደረጉ፡፡ በዚህም ምክንያት ጽሑፎቹን የሚመለከተው ሁሉ ሳያነባቸው ቀረ መልእክቱም ሳይደርስ ቀረ፡፡

አሁንም ስለ ጳጳሳቱ ሹመት ጉዳይ በእነዚያ ሁለት ጽሑፎች ቅኝት ብጽፈው ተመሳሳይ ችግር እንደሚገጥመው በመረዳት ማስተላለፍ የፈለኩት መልእክት፣ ማስተማር የፈለኩት ትምህርት መናፍቃኑን ጳጳሳት ጨምሮ ለሁሉም እንዲደርስ በመፈለግ ይሄንን መናፍቅ ሰውየ ኑፋቄዎቹን እንደማላውቅ ሆኘ ከሰውም ቢሆን ሰምቸ እንደማላውቅ በመግለጥ አንዳንዶቹን ከቤተክርስቲያናችን ባሕልና ሥርዓት አኳያ ብቻ የሚናገራቸውን የስሕተት ትምህርቶቹን በመተቸትና ትክክለኛውን የቤተክርስቲያናችንን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ባሕልና ሥርዓት በማስተማር ብቻ ሰውየው መሳሳቱንና መታረም መመለስ እንደሚገባው መልእክት በማስተላለፍ፤ ሰውየው ጵጵስናው እንደሚገባው በመግለጽ የጻፍኩት ጽሑፍ ከዚህ ቀደም የጻፍኳቸው ጽሑፎች ዕጣ ሳይደርስበት መልእክቱ እንዲደርሰው ለፈለኩት ሁሉ ለማድረስ ሞከርኩ፡፡ ያሰብኩትም ተሳክቶ መናፍቃኑ የደገፍኩ ስለመሰላቸውና ጽሑፉን እንዲነሣ ባለማድረጋቸው ማስተላለፍ የፈለኩት መልእክትና ማስተማር የፈለኩት ትምህርት እንዲደርሰው ለፈለኩት ሁሉ ማድረስ ቻልኩ፡፡ ይሄንንም ከደረሱኝ ግብረመልሶች ለመረዳት ችያለሁ፡፡

*መናፍቃኑ ከየድረገጹ ያስነሡትን "የቅዱስ ሲኖዶስን ስምና ሥልጣን የተጠቀመው የመናፍቃኑ መግለጫ!" የሚለውን ጽሑፍ ይዝ (ሊነክ) መጨረሻ ላይ አስቀምጥላቹሀለሁ አንብቡት፡፡*

ሁለተኛው ምክንያቴ ደግሞ በከዚህ ቀደሞቹ መናፍቃኑ ከየድረ ገጹ ከመለጠፋቸው እንዲነሡ ባደረጓቸው ጽሑፎች መናፍቃኑ በስደት ያለውን የቤተክርስቲያኗን ሲኖዶስና እዚህ ሀገር ቤት ያሉትንም (ቀኖናው ባይፈቅድላቸውም ፓትርያርክና ሲኖዶስ ነን ይላሉና) እነሱንም ሁለቱንም እንደተቆጣጠሩና ሲኖዶስን ሽባ አድርገው ሥራቸውን እንዳይሠሩ እንዳደረጉ፣ ቤተክርስቲያንን በአጭር ጊዜ ውስጥ በመናፍቃን እጅ እንድትገባ ሊያደርግ ከሚችል በታሪኳ ዓይታው በማታውቀው አደጋ ላይ ያለች መሆኗንና የቀራቸው ነገር ቢኖር "ትክክለኛው የቤተክርስቲያን አስተምህሮ… ነው!" በማለት የመናፍቃኑን አስተምህሮ በአዋጅ መንገር ብቻ መሆኑንና ከድል ጫፍ ላይ ያሉ መሆናቸውን በመግለጽ ቀጥሎ ያለውን ጥሪ፡-

""'…በዚህ አጋጣሚ እዚያው አሜሪካን ሀገር ላላቹሁት ካህናትና ምእመናን የተዋሕዶ ልጆች በሙሉ አጥብቄ ማሳሰብ የምፈልገው ጉዳይ ቢኖር ቤተክርስቲያን በዘመኗ ዓይታው በማታውቀው ከባድና እጅግ አሳሳቢ ፈተና ላይ ነው ያለችው፡፡ እዚህ ሀገር ቤት ያለነው ካህናትና ምእመናን የወያኔ ጳጳሳትና ካህናት ቤተክርስቲያንን መጫዎቻ መቀለጃ ሲያደርጓት በቆመችበት ደርቃ እንድትከስም ደም ስሮቿን ሲቆርጡና በርካታ አጋንንታዊ ተልእኳቸውን ሲፈጽሙባት ዓይተን መታገስ ባለመቻላችን ስንቃወም በጠባቂያቸውና አሠሪያቸው ወያኔ አፈሙዝ እየተቀጠቀጥን የመከራ ዓይነት እየዘነበብን እንድናርፍ ስለተደረግን ይሄው እንደምታዩን በዝምታ እየተመለከትን እንገኛለን፡፡

እናንተ እዚያ በነጻነት ሀገር ያላቹሁትና "ለመብታቹሁ ተጋደላቹሁ፣ ቤተክርስቲያናቹሁን ጠበቃቹሁ፣ ለቤተክርስቲያናቹሁ ተቆረቆራቹሁ፣ ተሟገታቹሁ" ብሎ አፈሙዝ የሚያዞርባቹሁና በእኛ ላይ እንደሆነው የመከራ ዓይነቶችን የሚያዘንብባቹሁ ኃይል ሳይኖር በቤተክርስቲያን ላይ ይሄንን ያህል ጉዳት ያደረሱብንን የመጥፋት አደጋን በቤተክርስቲያናችን ላይ የጋረጡትን መናፍቃን ጳጳሳትና ካህናትን መቃወም ማስወገድ ማባረር እየቻላቹሁ ቤተክርስቲያንን ያስበላቹሁት ምን ነክቷቹሁ ነው? ምእመናኑን አጠቃለው እስኪበክሉና እስኪረከቡ ነው ወይ የምትጠብቁት? መናፍቃኑ በቤተክርስቲያን ላይ እንዲህ ሲበረቱባት ሲያጠቋት ሲያጠፏት በዝምታ በማየታቹሁ በጌታ ዘንድ ከእነሱ እኩል ተጠያቂ የማትሆኑ ይመስላቹሀል? ጳጳሳት ለሃይማኖት የመቆርቆር ቤተክርስቲያንን የመጠበቅ ላቅ ያለ አደራና ኃላፊነት ቢኖራቸውም ቤተክርስቲያንን ከጥፋት የመጠበቅ ግዴታ ግን የአንድ ጳጳስና የአንድ ተራ ምእመን ግዴታ አንድ እንደሆነ አታውቁምን?

እናም እባካቹሁ በእነዚህ መናፍቃን ላይ ቆርጣቹሁ ተጠናክራቹሁ በመዝመት ቅዱስ አባታችንንና ሌሎቹንም ደጎና የሆኑትን ጳጳሳት ማለትም ሲኖዶሱን ነጻ አውጥታቹሁ የመናፍቃኑን እጅ በመቁረጥ ቤተክርስቲያንን ከጥፋት ታደጓት!!! አሁኑኑ ፈጥነን ያልተነሣን እንደሆነ ይሄንን አደጋ መቀልበስ በፍጹም እንደማንችል ሁሉም ሰው ሊያውቀው ይገባል!""'

ይሄንን ለካህናቱም ለምዕመናኑም አስቸኳይና አንገብጋቢ ጥሪ አምና ግንቦት ወር ላይ ሳቀርብ ደንገጥ ብሎ የተሰለፈ ሰው ስላልነበር አሁን የጳጳሳቱን ሹመት በተመለከተ በጻፍኩት ጽሑፍ መናፍቁን ወልደትንሣኤን እንደ ክርስቲያን ቆጥሬ ሹመቱ እንደሚገባው በመግለጽ ተኝቶ ቤተክርስቲያንን በማስበላት ላይ ባለው ሕዝበ ክርስቲያኑ ላይ ንዴት፣ ብስጭት፣ ቁጭት ለመቀስቀስና ከንዴት ብስጭት ቁጭቱ መነሣሣት እንዲፈጠር ለማድረግ ነበር፡፡ አሁንም ከደረሱኝ ግብረመልሶች እንደተረዳሁት ይሄም

ተሳክቶልኛል፡፡ አስቀድሜ እንደገለጽኩላቹህ ቀሪዎቹን ሁለት ምክንያቶችን አሁን አልነግራቹህም ካሰነበተን ጊዜው ሲደርስ የምነግራቹህ ይሆናል፡፡

እንግዲህ አምና ግንቦት ወር ላይ የሰጠሁት ማስጠንቀቂያ ማሳሰቢያና ጥሪ ጊዜው ደረሰና መናፍቃኑ ቅዱስ ፓትርያርኩን አቡነ መርቆሬዎስን ገድለው መንበራቸውን መልከጸዴቅ ተብለው ለሚጠሩት ጋኔን ሊያስይዙ በታላቅ ዝግጅት ላይ ይገኛሉ፡፡ እኒያ መልከጸዴቅ የተባሉት ጋኔን የሚሾሙት በኢትዮጵያ ለቤተክርስቲያን መጥፋት ሽግግር ላይ ጠቃሚ ሰው ስለሆኑ ነው እንጅ እሳቸው ዕድሜ ኖሯቸው ብዙ የሚያገለግሏቸው ሆነው አይደለም፡፡ ቅዱስ ፓትርያርኩ አቡነ መርቆሬዎስ በቅርቡ ተገድለው መንበሩን እኒህ ጋኔን እንዲይዙ የተወሰነውም በዚህ ምክንያት ነው ጋኔኑ ከማርጀታቸው የተነሣ ሊያመልጡ ይችላል ተብሎ ስለተፈራ፡፡

በሌሎች አኃት በሚባሉት አብያተክርስቲያናት እንደተደረገው ሁሉ የኢትዮጵያ ቤተክርስቲያንንም አስተምህሮዋን ቀይሮ እንዳለች የመውረስ እንቅስቃሴ እንዲህ በተራ በጥቂት ኢጋንንት ከነነፍሳቸው በለበሷቸው የሰይጣን ሽንቶች የሚከወን ሳይሆን ከእነኝህ የሰይጣን ሽንቶች ዘመቻና እንቅስቃሴ ጀርባ ሆነው እነኝህን አሜሪካ ባለው ቅዱስ ሲኖዶስ ያሉ መናፍቃን ጳጳሳትን፣ ሀገር ቤት ደግሞ አባ ጳውሎስን አባ ማትያስንና ሌሎች መናፍቃን ጳጳሳትንና ካህናትን ሲያንቀሳቅሱ የቆዩትና እያንቀሳቀሱ ያሉትም አሜሪካና እንግሊዝ ያሉ የፕሮቴስታንት ድርጅቶችና ቫቲካን ናቸው፡፡ እነኝህ የመናፍቃን ድርጅቶች ደግሞ በመንግሥቶቻቸውና በወያኔ ይደገፋሉ፡፡

የዚህን የተቀናጀ የመናፍቃን አደገኛና እጅግ አስፈሪ አሳሳቢ ዘመቻ ሴራ ከመፍራቱና ከሌሎችም ሁኔታዎች የተነሣ የሚያውቀውንና የያዘውን ሁሉ ለሕዝብ ይፋ አያድርገው እንጅ ማኅበረ ቅዱሳን የሴራውን ከፊል መረጃ ያውቃል ሰነዶችንም ይዟል፡፡ ከማኅበረ ቅዱሳን ባልተናነሰ አንዳንድ ታላላቅ ግለሰቦችም መረጃዎቹ አሏቸው፡፡

በቅዱስ ሲኖዶስ (አሜሪካ ባለው ማለቴ ነው) ከዚህ ቀደምና አሁን በተደረጉት የኤጲስ ቆጶሳትና የጳጳሳት ሹመት ውስጥ ጵጵስና እንዲሾሙ የተደረጉት መናፍቃን በሙሉ ጎንደሬዎች ብቻ እንዲሆኑ የተደረገውም ሆን ተብሎ ነው፡፡ ጎንደር ከጥንት ጀምሮ ለኢትዮጵያ ቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት ማዕከል በመሆኗና ቤተክርስቲያንን የመለወጥ የመናፍቃኑ ጥቃትም ያነጣጠረው በዚህ የቤተክርስቲያን ትምህርተ ሃይማኖት መሠረት ላይ በመሆኑ ይሄንን ለመምታትና ለማጥፋት በማሰብ የተገረገ ነው፡፡

እንግዲህ የእግዚአብሔርን አላውቅም በእኔ ግምት ግን ሀገር ቤትም ሆነ አሜሪካ ያለነው ሕዝበ ክርስቲያን ድፍረቱ፣ ቁርጠኝነቱ፣ ጽናቱ፣ እልሁ፣ ቀናኢነቱ፣ መታመኑ፣ መሥዋዕትነት ለመክፈል ዝግጁ ሆነን እንዲህ በባዕዳን መንግሥታት በመናፍቃን ድርጅቶችና በወያኔ የተቀናጀውንና የተደራጀውን ዘመቻ ተቋቁመን ቅድስት ቤተክርስቲያንን

መታደግ መቻላችንን በእጅጉ ስለምጠራጠር ይሄንን የቤተክርስቲያን አደጋ ፈርተው እንደበታቸውን ላይናገር በአርምሞ በመዝጋት ሱባኤ ከያዙ ዓመታት ያስቆጠሩት ቅዱስ አባት ፓትርያርክ መርቆሬዎስ በቅርቡ በእነኝህ የሰይጣን ሽንቶች ተገድለው ሠማዕት መሆናቸው፤ መንበራቸውን መናፍቁ መልከጸዴቅ መያዙና "ትክክለኛው የቤተክርስቲያን አስተምህሮ… ነው!" ተብሎ የመናፍቃኑ የኑፋቄ አስተምህሮ በቤተክርስቲያናችን አውደ ምህረት ላይ መታወጁ፣ እዚህ ሀገር ቤትም አሜሪካም ያለው የቤተክርስቲያን መዋቅር ሙሉ ለሙሉ በመናፍቃኑ ቁጥጥር ስር መውደቁ የሚቀር አይመስለኝም፡፡ ሁሉንም ሩቅ ሳይሆን በቅርብ የምናየው ይሆናል፡፡

ተኝተህ የራስህን ድርሻ፣ የተጣለብህን ክርስቲያናዊ ግዴታና ኃላፊነት ሳትወጣ "አይ! እግዚአብሔር ቤተክርስቲያንን ፈጽሞ አይረሳም ይጠብቃታል! እስከዚህ ድረስ ቤተክርስቲያንን ለአጋንንት አሳልፎ አይሰጣትም!" በማለት እግዚአብሔርን ለመሸንገል የምትሞክርና እራስህን የምታጃጅል ሁሉ እንዲያ እያልክ መተኛትህ፣ ኃላፊነትህን ግዴታህን አለመወጣትህ መናፍቃኑን ለዚህ ድል አብቅቷልና በአምላክ ፊት እንደምትየቅበት እንድታውቅ!

አንጋት አብያተክርስቲያናትን ጨምሮ ጥንት ከቤተክርስቲያን እየተገነጠሉ በጠፉት ሀገራት ዘንድ ቤተክርስቲያን የጠፋችው እግዚአብሔር ለእነሱ ስላልነበረ፣ ስለነሱ ስለማያውቅ አልነበረም፡፡ በእነዚህ ሀገራት ያሉ ካህናትና ምእመናን የድርሻቸውን፣ የሚጠበቅባቸውን፣ ኃላፊነታቸውን፣ ግዴታቸውን ስላልተወጡና አሁን አንተ እንደምትለው እያሉ እራሳቸውን ለማታለል እግዚአብሔርን ለመሸንገል ስለሞከሩ እንጅ፡፡

ክርስቲያናዊ ግዴታን፣ ኃላፊነትን፣ አደራን፣ ድርሻን ላለመወጣት ለመሸሽ ሌላም የሚጠቀስ ሰበብ አለ፡፡ ወያኔ በቤተክርስቲያን ላይ የሚያደርሰውን ግፍ በደልና ጥፋት ተቃወሙ ሲባሉ **"**ፖለቲካ ነው**!"** ይላሉ፡፡ ወያኔና የወያኔ ቅጥረኛ ካህናት ለወያኔ ጥቅም የሚያደርጉትን ሁሉ ሲያደርጉ ግን ፖለቲካ አይደለም፡፡ **"**ይሄ ይሄ ነገር ፖለቲካ ነው እኛ ደግሞ መንፈሳዊያን ነን አናደርገውም**!** ቤተክርስቲያንም አይገባብንም**!"** ካሉ ወያኔና የወያኔ ቅጥረኛ ካህናት ጥቅማቸውን የሚያስጠብቅና ቤተክርስቲያን የሚጎዳ ፖለቲካቸውን ቤተክርስቲያን ላይ በመፈጸም ቤተክርስቲያንን ሲያጠፉ በዝምታ ሊመለከቱ ባልተገባ ነበር፡፡ ነገሩ ግን ይሄንን የሚሉት ኃላፊነትን ላለመወጣትና ለመሸሽ በመሆኑ ይሄንን ሊያደርጉ አልቻሉም፡፡

እናም በእነኝህ በእነኝህ ችግሮቻችን ዓይናችን እያየ ቤተክርስቲያንን ለአጋንንት ልናስረክብ ነው፡፡ "እኔ እያለሁ! ቆሜ ነው ሳልሞት!" የምትል የክርስቶስ አርበኛ ካለህ፡፡ ቤተክርስቲያንን ለዚህ ያበቋትን ጳጳሳት ነን የሚሉ የውሸት አጋንንት ጳጳሳትንና አጫፋሪዎቻቸውን እስከ መግደል እንኳን ድረስ ብትበረታ ለዚህ አርበኝነትህ ከእግዚአብሔር ዘንድ ዋጋና ክብር ታገኝበታለህ እንጅ "ነፍስ አጠፋሁ ኩነኔ ሠራሁ!" ብለህ መሳቀቅ እንደሌለብህ አጥብቄ ላስገነዝብህ እወዳለሁ፡፡

እናት አባቶቻችን ይሄንን ጠንቅቀው ያውቁታል፡፡ አድዋ ላይም ሆነ ከዛም በፊት ከዚያም በኋላ ድንበር ገፍቶ ከመጣ ጠላት ጋር እየተናነቁ ሲገሉም ሲሠውም ኃጢአት እያደረጉ እንደሆነ እያሰቡ ይመስላቹሀል ያንን ያደርጉ የነበሩት? ካህናቱስ የቃልኪዳኑን ታቦት ተሸክመው አብረው በመሰለፍ "እግዚአብሔር ይፍታሕ! ግባ በለው!" እያሉ እያጀገኑ ሲያዋጉ የማይገባና ኃጢአት የሆነ ነገርን እያደረጉ ይመስላቹሀል እንዴ? እንዳይመስላቹህ!!!

በእርግጥ ጥቂት ያልሆኑ ይሄንን ያደረጉ እናት አባቶቻችንም የሀገር ጉዳይ ሆኖባቸው ስላልቻሉ "አትግደል!" የሚለውን የእግዚአብሔርን ሕግ በመተላለፍ እንዳደረጉት ያስቡ ነበር እንጅ ያደረጉት ነገር ኃጢአት እንዳልሆነ በማሰብ አያደርጉትም ነበር፡፡ እውነቱ ግን የእግዚአብሔር ቃል ይሄንን እንዲያደርጉ ይፈቅድላቸዋል፡፡ እንዴት? ብትሉ ነገሩ እንዲህ ነው፡-

የእግዚአብሔር ቃል እንዲህ ይላል "ነፍስ ሁሉ በበላይ ላሉት ባለ ሥልጣኖች ይገዛ። ከእግዚአብሔር ካልተገኘ በቀር ሥልጣን የለምና፤ ያሉትም ባለ ሥልጣኖች በእግዚአብሔር የተሾሙ ናቸው። ስለዚህ ባለ ሥልጣንን የሚቃወም የእግዚአብሔርን ሥርዓት ይቃወማል፤ የሚቃወሙትም በራሳቸው ላይ ፍርድን ይቀበላሉ። ገዥዎች ለክፉ አድራጊዎች እንጂ መልካም ለሚያደርጉ የሚያስፈሩ አይደሉምና። ባለ ሥልጣንን እንዳትፈራ ትወዳለህን? መልካሙን አድርግ ከእርሱም ምስጋና ይሆንልሃል፤ ለመልካም ነገር ለአንተ የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና። በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና" ይላል ቅዱስ ቃሉ ሮሜ. 13፤1-4

ይሄ ማለት ምን መሰላቹህ? እንዲህ ሲል ለሁሉም ለመጣ ለሔደው ሁሉ ብቻ ገዥ ሆኖ ለተሾመው ሁሉ ሰጥ ለበጥ ብላቹህ ተገዙ ማለት ነው የሚመስላቹህ? በፍጹም! እንደዛ ማለቱ አይደለም:: በሃይማኖት ለሚመስሏቹህ፣ ሃይማኖታቹህን ሀገራቹህን ለሚጠብቁላቹህ፣ ከጠላቶቻቹህ ጋር ለማይተባበሩ፣ እንደ ወያኔ ለሀገርና ለቤተክርስቲያን ጠላቶች ቅጥረኛ ሆኖ ሀገራቹህንና ሃይማኖታቹህን ለማያጠፉ ማለቱ ነው፡፡

አለዛማ እኮ እነ ዲዮቅልጥያኖስን፣ እነ መክስምያኖስን በሀገራችን ደግሞ እነ ዮዲት ጉዲትን፣ እነ ግራኝ አሕመድን፣ እነ ፋሽስት ጣሊያንን እየተቀበልንና አድርጉ ያሉንን እየፈጸምን ማለትም "ሃይማኖት ለውጡ! ጣዖት አምልኩ!" ሲሉ እሽ ብለን እየለወጥን ጣዖት እያመለክን "ምግባራቹህን ጣሉ!" ሲሉን እሽ ብለን ምግባራችንን እየጣልን ግብረ አረሚን እየፈጸምን መገዛት ነበረብን ማለት ሊሆን እኮ ነው፡፡ ይሄ ደግሞ እግዚአብሔርን የሚያስቆጣ፣ የሚያስቀይም፣ የሚያስከፋ የገሃነም ፍርድንም የሚያሰጥ የጥፋት ድርጊት እንጅ እግዚአብሔርን የሚያስደስት የጽድቅ ሥራ እንዳልሆነ ታውቃላቹህ ብየ እገምታለሁ፡፡

እናም እነኝህ እኛን የሚመስሉ ገዥዎቻችን ወይም መንግሥታቶቻችን ጠላትንም ሆነ በባንዳነት አድሮ የሀገርንና የሃይማኖትን ጥቅም የሚጋፋውን የሚጻረረውን፣ ለሞት የሚያበቃ ወንጀል የፈጸመውን ሁሉ በሞት ቢቀጡት ኃጢአት አይሆንባቸውም ነው ያለው፡፡

በጠቀስኩላቹህ ጥቅስ ላይ ቁጥር አራት ላይ ያለውን ቃል ልብ ብላቹህታል? "...በከንቱ ግን ሰይፍ አይታጠቅምና ክፉ ብታደርግ ፍራ፤ ቍጣውን ለማሳየት ክፉ አድራጊውን የሚበቀል የእግዚአብሔር አገልጋይ ነውና" ነው ያለው፡፡ አያቹህ? ክፉ አድራጊውን በመበቀሉ

በመቅጣቱ "የእግዚአብሔር አገልጋይ ነው" ተባለ እንጅ ነፍስ አጥፍቷል ተብሎ ኃጢአተኛ ነው አልተባለም፡፡ ድርሳነ ሚካኤልም ይሄንን ይዞ ነው "ወለ ሕዝባዊያንሰ ብውኅ ሎሙ እም ኀበ እግዚአብሔር ከመ ይቅትሉ በፍትሕ ለዘይደልዎ ሞት! ከሕዝብ ወገን የሆኑት (ክህነት የሌላቸው) ሞት ለሚገባው በፍትሕ ይገድሉ ዘንድ ከእግዚአብሔር ዘንድ ተፈቅዶላቸዋል!" ያለው፡፡

ለዚህም እኮነው ዐፄ ምኒልክ አድዋ ሲዘምቱ በአዋጃቸው ላይ ኃጢአት እንዳልሆነ በተረዳ ልበ ሙሉነት "… ሀገር የሚያጠፋ ሃይማኖት የሚለውጥ ጠላት!" ሲሉ አዋጃቸውን ያስነገሩትና ሕዝባቸውን ያዘመቱት፡፡ በዚህ ምክንያት የሚደረግ ጦርነት ጽድቅ እንጅ ኃጢአት እንዳልሆነ ስለሚያውቁ፡፡ አለዛማ መግደል ኃጢአት ነው እያሉ ሀገርንም ሃይማኖትንም አስረክበው ቁጭ አይሉም ነበር እንዴ? ቅዱስ ጊዮርጊስም ከአምላክ ተልኮ የተራዳን እኮ የሀገርንና የሃይማኖት ጠላትን መግደል ኃጢአት ባለመሆኑ ነው፡፡ ጣሊያኖች ምስክርነት ሰጥተው የለም እንዴ! ከአርበኞች አንዱ መስሏቸው ጦርነቱ ካለቀ በኋላ የጣሊያን ምርኮኞች "ስንተኩስበት የማይሞተው በነጭ ፈረስ ላይ ሆኖ በሰይፉ እየቀላ ሲፈጀን የነበረው ሰውየ ማን ነው? የታለ?" ብለው ነበር፡፡

ክርስትና "እንደበግ እየተነዳ እራስን ለእርድ ማቅረብ" ማለት የሚመስላቹህና ይሄንንም የምትሰብኩ አባቶችና ወንድሞች ካላቹህ እርማት ውሰዱ፡፡ ክርስትና እንዲህ አይደለም! በእርግጥ ክርስትና የፍቅር ሃይማኖት ነው፡፡ ይሄ ማለት ግን "በፍቅር ካልሆነ በግፍ በኃይል የሚያደርገው አንድም ነገር የለም!" ማለት እንጅ በግፍ ለሚመጡብት አረማውያን ለመሥዋዕት እንደሚነዳ በግ በዝምታ ወደ መታረጃው የሚነዳ መንጋ ነው ማለት አይደለም፡፡

አዎ! ክርስቶስ በወንጌሉ ከፉውን በክፉ እንዳንቃወም አዞናል፣ ቀኝ ጉንጫችንን ለሚመታን ግራችንንም እንድናዞርለት፣ እጀ ጠባባችንን ለሚወስድብን መጎናጸፊያችንን እንድንጨምርለት፣ አንድ ምእራፍ እንድንሔድ ለሚያስገድደን ሁለተኛውን ምእራፍ ፈቅደን እንድንሔድለት አዞናል፡፡ ይሄንን ሲል ግን ጠላት ዲያብሎስ አንድ በግ ሲነጥቃቹህ ሁለተኛውን ጨምሩለት፣ ቤተክርስቲያንን ሊውጥ አፉን አስፍቶ ሲከፍት አመቻችታቹህ አጉርሱት፣ ጥምቀተ ባሕሩን ሲወስዱባቹህ መስቀል አደባባዩንም ጨምሩላቸው፤ ይሄንና ይሄንን የመሰለ ጅልነት አድርጉ ማለቱ እንዳልሆነ ሁላችንም መረዳት የምንችል ይመስለኛል፡፡

ስለሆነም ይህ አምላካዊ ትዕዛዝ ቅድመ ሁኔታና መቸት አለው ማለት ነው፡፡ ባጭሩ ሃይማኖትንና ሀገርን በተመለከተ ጉዳይ ላይ ይሄንን አምላካዊ ትዕዛዝ እንድንፈጽም ፈጽሞ አልታዘዝንም፡፡ የሚመስላቹህና ሳይገባቹህ ሰው ጅል እንዲሆን የምትሰብኩ አባቶችና ወንድሞች በክርስትና ላይ ያላቹህን የተሳሳተ መረዳት ነውና አስተካክሉ!

"እንዲህ ዓይነት እንደ አባቶቻችንና እናቶቻችን ያለ ልብ የለኝም ፈሪ ነኝ!" የሚል ደግሞ ቢያንስ ቢያንስ በጾም በጸሎት በስግደት ወደ ፈጣሪ በመጮህ ግዴታና ኃላፊነቱን መወጣት ይኖርበታልና ይሄንን በማድረግ እንተጋ ዘንድ አጥብቄ ማሳሰብ እወዳለሁ፡፡ እንዲያው አንዱንም ማድረግ ሳንችን ከንፈር መጣጮች ብቻ ከሆንን ግን ወዮ ለራሳቹህ ፍርድ ይተብቃቹሀል!!!

የአባቶቻችን አምላክ ልዑል እግዚአብሔር ነገራችንን፣ እጣ ፋንታችንን እንደ ኢጋንንት ምኞትና ፍላጎት እንዳያደርግብን፣ እንዲያበረታን፣ እንዲያጸናን፣ እንዲያጀግነን፣ ግዴታ ኃላፊነታችንን እንድንወጣ እንዲያስችለን ቅዱስ ፈቃዱ ይሁንልን አሜን!!!

http://www.zehabesha.com/amharic/archives/48210

የላይኛው ይዞ (ሊንክ) ካልከፈተ የታችኛውን ይዞ (ሊንክ) ይጫኑና ከፍተፍው ያንብቡ!

http://www.ethiopanorama.com/wp-content/uploads/2015/11/Sinod-1-1.pdf

ሠዓሊ አምሳሉ ገ/ኪዳን አርጋው

amsalugkidan@gmail.com

***http://www.ethiopanorama.com***